# የሃይማኖትና እምነት ድርጅቶች፣ ማህበራትን ለመመዝገብና ተዛማጅ አገልግሎት ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 19/2012

**????? ?? ??? ?? ?? ? ??? ?? ??? ? ?????? ?? ?? ?**

**??? ? ? ??**

## **? ???**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ14/1/ሽ/ቀ/ መሰረት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለመወጣት፣

የሃይማኖትና እምነት ድርጅቶችንና ማህበራትን ምዝገባና ተዛማጅ አገልግሎቶች አሰጣጥን ህጋዊ መሰረት ለማስያዝ፣ ከክልሎች ጋር ያለውን የስራ ግንኙነት ውጤታማና ቀልጣፋ ለማድረግ፣ የሃይማኖትና እምነት ተቋማት አመሰራረት ሂደት ለተለያዩ ችግሮች አጋላጭነቱና ተጋላጭነቱ እየጎላ በመምጣቱ በህጋዊ መንገድ መከላከል በማስፈለጉ፣ህገ-ወጥ የውጪ ጣልቃ ገብነትን ለከላከልና ለመቀነስ፣ ከአምልኮና ስብከት ጋር በተያያዘ የሚታዩ ችግሮችን ስርአት ማስያዝ በማስፈለጉ፣ የሰብኣዊ ልማት/የበጎ አድራጎት/ ስራዎችን ከመንፈሳዊ ስራዎች መለየት አስፈላጊ በመሆኑ፣አዳዲስ የሃይማኖት፣ የእምነት ድርጅትና ማህበርን ከመመስረት ጋር የተያያዙ የመልካም አስተዳር ጥያቄዎች በከፍተኛ ሁኔታ በመበራከቱና ህጋዊ ስርዓት ማስያዝ በማስፈለጉ፣ የሐይማኖት ተቋማት ለሀገራችን ሠላም፣ ልማት እና እድገት የሚያበረክቱትን አስተዋፅዖ ግምት ውስጥ በማስገባት ይህንኑ በተጠናከረ ሁኔታ ለማስቀጠል ነው፡፡

በአጠቃላይ በህገ መንግስቱ የተረጋገጠውን የሐይማኖት ነፃነት፣ እኩልነት፣ የመንግስትና የሐይማኖት መለያየት እና የመደራጀት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ አሰራራቸው ከህገ-መንግስቱና ከሌሎች የሃገሪቱ ህጎች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ እንዲቀጥልና በግልፅነትና ተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ አገልግሎት ለመስጠትና ለማግኘት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## 1. ?? ? ???

ይህ መመሪያ "የሐይማኖት ተቋማትን ?? ? ??? ?? ??? ? ????? ? ?? ??? የወጣ መመሪያ" ቁጥር 19/2012 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ????

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ ዓላማ ፤

1. «**ሚኒስቴር** እና **ሚኒስትር**» ማለት፡- እንደቅደም ተከተሉ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴርና ሚኒስትር ነው፡፡
2. «**የሐይማኖት ተቋም**» ማለት፡- ሰዎች የመረጡትና የተቀበሉትን ሐይማኖት ይዘው በይፋ ለማምለክ፣ ለመከተል፣ ለመተግበር፣ ለማስተማር፣ ለመግለጽ ወይም ለማስፋፋት እንዲያስችላቸው ያደራጁትና ዓላማው ለትርፍ ያልሆነ በሚመለከተው አካል ተመዝግቦ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው ቤተ ዕምነት፣ መንፈሳዊ የትምህርት ተቋም፣ ማህበር ፣ሚኒስትሪ ፣ፌሎሺፕ ፣አገልግሎት እና መሰል አደረጃጀቶች ሲሆኑ የእምነት ተቋምንም ያካትታል፡፡
3. «**መተዳደሪያ ደንብ**» ማለት፡- የሐይማኖት ተቋሙ የተቋቋመለትን ወይም ሊያራምደዉ የሚፈልገዉን ዓላማ በተመለከተ፣ ስለአባልነት ፣መብትና ግዴታ፣ ስለአስተዳደራዊ መዋቅሩና ተግባሩ፣ ስለማኅበሩ መዋሃድ፣ ህብረት መፍጠር፣ ህጋዊ ሰውነት ማጣት፣ ስለንብረቱ ሁኔታ፣ስለደንብ መሻሻልና በአጠቃላይ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚገልፅና የሚወስን ሰነድ ነው፡፡
4. «**ሀገር በቀል የሐይማኖት ተቋም**» ማለት፡-ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ በሆኑ ሰዎች የሚመሰረትና የሚመራ የሐይማኖት ተቋም ማለት ነው፡፡
5. «**የውጭ ሀገር የሐይማኖት ተቋም**» ማለት በውጭ ሀገር ዜጎች የሚመሰረት ወይም በውጭ ሃገር ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ የከፈተ የሐይማኖት ተቋም ማለት ነው ፡፡
6. «**ልማት**» ማለት፡- በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ተመዝግበው የሚከናወኑ የበጎ አድራጎት ተግባራት ማለት ነዉ፡፡

7. **«የበላይ አካል**»፡- ማለት እንደየ ሃይማኖት ተቋሙ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ስልጣን የተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል ማለት ነው፡፡
8. **«ቦርድ**» ማለት ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ወይም ተመሳሳይ ስልጣን ለተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ አካል የሆነ የአመራር አካል ነው፡፡
9. **«ተዛማጅ አገልግሎት**» ማለት በሃይማኖት ተቋማቱ ጥያቄ መሰረት ለባንክ፣ ለህትመት ስራዎች፣ ለሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፣ ለውልና ሰነዶች ማረጋገጫ ፅ/ቤት ለፌደራል መ/ቤቶች፣ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፣ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሚፃፉ ደብዳቤዎች ማለት ነው፡፡
10. **"የአገልግሎት ክፍያ**"፡- ማለት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሃይማኖት ተቋሙን ለመመዝገብና ለሚሰጣቸው ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባጸደቀው የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ ሠንጠረዥ መሠረት የሚፈጸም የአገልግሎት ክፍያ ነው፡፡
11. **«ኅብረት**» ማለት፡- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑና ቀደም ሲል የየራሳቸው ህጋዊ ሰውነት ያላቸው የሐይማኖት ተቋማት የቀድሞ ህልውናቸውን እንደያዙ የጋራ ሐይማኖታዊ ዓላማቸውን ለማሳካት አንድ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የሐይማኖት ተቋም መመስረት ነው፡፡
12. **«ውህደት**» ማለት፡- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑና ቀደም ሲል የየራሳቸው ህጋዊ ሰውነት የነበራቸው የሐይማኖት ተቋማት የቀድሞ ህልውናቸውን በመተው የጋራ ሐይማኖታዊ ዓላማቸውን ለማሳካት አንድ ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የሐይማኖት ተቋም መመስረት ነው፡፡
13. **«ክልል**» ማለት፡- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት በአንቀጽ 47 የተመለከቱትን አባል የሆኑ ክልሎችን ፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ አሰተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡
14. **«የበጀት ዓመት**» ማለት፡- እንደየሐይማኖት ተቋማቱ ፍላጎትና አጠቃቀም በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ወይም እ.ኤ.አ አቆጣጠር ከጃንዋሪ 1 እስከ ዲሴምበር 31 ያለው ጊዜ ወይም የሃይማኖት ተቋሙ እንደየ አስተምህሮው የሚከተለው የዘመን አቆጣጠር ነው፡፡

15. **«አዋጅ»** ማለት፡- የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ□ን አዋጅ ቁጥር 916/2008 ማለት ነው፡፡

16. **«ሰው»** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የህጋዊ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

17. በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
   - ሀ/ በዘጠኙ ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚሰሩ ሀገር በቀል የሐይማኖት ተቋማት፣
   - ለ/ በውጭ ሃገር ዜጎች የተመሰረቱ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ አቋቁመው በሚሰሩ የውጭ ሀገር የሐይማኖት ተቋማት፣
2. ይህ መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡
   - ሀ/ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት፤
   - ለ/ በሌላ ህግ በሚሸፈኑ ሌሎች ድርጅቶችና ማኅበራት፡፡

## 4. የሚኒስቴሩ ተግባራት

ለሚኒስቴሩ በአዋጁ ቁጥር 916/2008 አንቀጽ 14/1/ሸ/ቀ/ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር መነሻ በማድረግ ይህን መመሪያ በተመለከተ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

በዚህ መመሪያ መሰረት የሐይማኖት ተቋማትን፡-

1. መመዝገብ፣ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፣ ዕድሳትና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የመስጠት፤
2. የሚያቀርቡትን የመተዳደሪያ ደንብ ከህገ መንግስቱና ሌሎች የሃገሪቱ ህጎች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
3. በሃይማኖት ሽፋን የሚደረግ አክራሪነትና ፅንፈኝነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ያስፈፅማል
4. የሃይማኖት መሪዎች እንዲሁም ተከታዮቻቸው በሐይማኖት ነክ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎችና በሌሎች የሃገሪቱ ህጎች ላይ ግንዛቤ እንዲይዙ ማድረግ፣

5. በሃይማኖት ተቋማት ውስጥና መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በራሳቸው ወይም እንደአስፈላጊነቱ ከሌሎች አካላት ጋር በመሆን መፍትሔ ማፈላለግ፤
6. ምዝገባ፣ የስምና የዓርማ ለውጥ፣ውህደት፣ኅብረት እና ህጋዊ ሰውነት ማጣትን በሚመለከት በጋዜጣ እንዲያሳትሙ ማድረግ፣
7. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ክፍያ ማስከፈል፣
8. ከህገ መንግስቱ፣ ከሌሎች የሃገሪቱ ህጎች፣ከዚህ መመሪያና ከመተዳደሪያ ደንባቸው ጋር በሚቃረን ሁኔታ የሚሰሩ ተቋማትን በዚህ መመሪያ መሰረት የምዝገባ ምስክር ወረቀታቸውን ማገድ፣መሰረዝ በተጨማሪም አግባብነት ባላቸው ህጎች መሠረት እንዲጠየቁ ማድረግ፤
9. ምትክ ማስረጃ መስጠት፣
10. ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ፣
11. ሌሎች ከዚህ መመሪያ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን፡፡

## ክፍል ሁለት

## ምስረታ፣ ምዝገባ እና ስያሜና ዓርማ/ምልክት አጠቃቀም

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ሃገር በቀል የሐይማኖት ተቋማት

### 5. ምስረታ

1. የሐይማኖት ተቋም ለመመስረት ፍላጎት ያላቸው መሥራቾች ለሚኒስቴሩ በማመልከት ምስረታቸውን ማካሄድ ይችላሉ፡፡
2. የሐይማኖት ተቋም ለመመስረት፡-

   ሀ/ ህጋዊ ተግባራትን ለመፈጸም ችሎታ ያላቸው ሰዎችና

   ለ/ ዓላማው ሐይማኖታዊ ተግባራትን ለማከናወን መሆን አለበት፡፡
3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ያመለከቱ መሥራቾች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ከተመሠረቱበት ቀን ጀምሮ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ መመዝገብ አለባቸው፡፡ ምዝገባውን በተቀመጠው ጊዜ ያላጠናቀቀ እንዳልተመዘገበ ተቆጥሮ በሚኒስቴሩ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ማግኘት አይችልም፡፡

### 6. ለምዝገባ ማመልከት

1. በሐይማኖት ተቋምነት ምስረታቸውን ያጠናቀቁና ህጋዊ ተግባራትን ለመፈጸም ችሎታ ያላቸው

ሀ/ የሚመዘገበው ቤተ ዕምነት ከሆነ የመስራቾች ቁጥር ቢያንስ _አንድ ሽህ ሰዎች፣_

ለ/ የሚመዘገበው በማኅበር፣ በሚኒስትሪ፣ በፌሎሺፕ፣ በአገልግሎትና መሰል አደረጃጀት ከሆነ የመስራቾች ቁጥር ቢያንስ _አምስት መቶ ሰዎች_ መሆን አለባቸው፡፡

ሐ/ በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ1 ሀ እና ለ የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀደም ሲል በማኅበር፣ በሚኒስትሪ፣ በፌሎሺፕ፣ በአገልግሎትና መሰል አደረጃጀት የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ተሰጥቷቸው ሲሰሩ የነበሩና ወደ ቤተ-እምነትነት ለማሳደግ ሲፈልጉ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ሀ የተገለፀውን ማሟላት አለባቸው

መ/ መስራቾቹ ህገ መንግስቱን አክብረው እና በሰላም አብሮ የመኖር እሴትን ጠብቀው የሚንቀሳቀሱ አካላት ለመሆናቸው ከክልላቸው የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ፣

ሠ/ ከላይ በፊደል ሀ እና ለ የተጠቀሱት መስራቾች ቀደም ሲል ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አቻ የሃይማኖት ተቋም መስራች ወይም አባል ያልሆኑ መሆን አለባቸው፡፡

2. ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቀደም ሲል ተመዝግበው ህጋዊ ሠውነት ያገኙ የሐይማኖት ተቋማት ሕብረት ለመመስረት ወይም ለመዋሃድ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ ይችላሉ፡፡

## 7. ምዝገባ

1. ሚኒስቴሩ አንድን የሐይማኖት ተቋምን የሚመዘግበው፡-

ሀ/ ከማመልከቻው ጋር የቀረቡት መመስረቻ ጽሁፍና መተዳደሪያ ደንብ በመስራቾች ቃለ ጉባኤ የተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ፣

ለ/ የተቋቋሙለት ዓላማ ከህገ መንግስቱና ከሀገሪቱ ህጎች ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ፣

ሐ/ ከሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ባህል፣ሞራል እና ሥነ-ምግባር ጋር የማይጋጭ መሆኑን በማረጋገጥ፣

መ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

2. ለምዝገባ መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

ሀ. የሐይማኖት ተቋሙ ሊጠራበት የተፈለገው ስም እንዲሁም ዓርማ/ምልክት

ለ. የሃይማኖት ተቋሙ የተቋቋመበት መመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ፣

ሐ. ሚኒስቴሩ በሚያቀርበው ፎርም መሠረት የሚሞላ ስለመሥራቾች አጭር መረጃ፣

መ. የመስራቾቹን ማንነት የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ/የወረዳ ነዋሪነት መታወቂያ፣

ሠ. የሐይማኖት ተቋሙ ዋና አድራሻና ቅርንጫፍ የሚከፍትባቸው ቦታዎች ዝርዝር ፣

ረ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ቋሚ የአመራር አካላት እስኪሰየሙ ድረስ እስከ ስድስት ወር የሚያገለግሉ ጊዜያዊ አመራሮች የተመረጡበትና ለመመዝገብ የወሰኑበት ቃለ ጉባኤ፣

ሰ. ማህበር /አገልግሎት/ ከሆነ እንደየ እምነቱ ከሚመለከተው እናት ተቋም /የሃይማኖት ድርጅት/ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ፣

3. ቀደም ሲል ህጋዊ ሰውነት ያላቸው የሐይማኖት ተቋማት ሕብረት ለመመስረትና ለመዋሃድ ሲፈልጉ በህጋዊ መንገድ ሕብረት መመስረታቸውንና መዋሃዳቸውን የሚገልጽ የተናጠልና የጋራ የተቋሙ የበላይ አካል ውሳኔ የሰጠበት ቃለ ጉባዔና ለምዝገባ የሚያስፈልጉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 "ሀ"፣"ለ"፣"ሠ" እና "ረ" የተመለከቱትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

4. የሐይማኖት ተቋሙ ከተመዘገበ በኋላ በማናቸውም ምክንያት ሳይሟሉ የቀሩ ጉዳዮች ከተገኙና ከተረጋገጡ ሚኒስቴሩ በሃያ የስራ ቀናት ውስጥ እንዲያሟሉ ያደርጋል።

5. በንዑስ አንቀፅ 4 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ ለምዝገባ ያቀረባቸው ሰነዶች ወይም መረጃዎች ሕገ ወጥ ሆነው ከተገኙና ከተረጋገጡ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ይሰርዛል፣ እንደ ሁኔታው አግባብ ባለው ህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል።

6. በአንቀፅ7 በንኡስ አንቀፅ 2 የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ከዚህ በፊት ሳይመዘገቡ ሃይማኖታዊ ተግባራቸውን ሲፈፅሙ የነበሩ የሃይማኖት ተቋማት ይህ መመሪያ በወጣ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በተቋሙ የበላይ አካል አማካኝነት ቀርበው ይመዘገባሉ።

7.በህገ-መንግስቱ መሠረት ቀደም ሲል ተመዝግበው ያሉ የሃይማኖትና ዕምነት ተቋማት በተመዘገቡበት ህግ መሠረት የተገኘ መብት ወይም የተጣለባቸው ግዴታ ይህን መመሪያ እስካልተቃረነ ድረስ ባሉበት ይቀጥላሉ፡፡

## 8. አደረጃጀት

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፤-

1. ሐይማኖታዊ ዓላማውንና ተግባሩን የሚገልጽበትና የሚሰራበት አደረጃጀት ወይም መዋቅር ሊኖረው ይችላል፡፡
2. እንደማንኛውም ሰው ህጋዊ ተግባራትን ለመፈጸም የሚያስችል የሐይማኖት ተቋሙን የበላይ አካላት፣ አስተዳደርና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ የሚሰጡ አካላትን የሚያሳይ አስተዳደራዊ መዋቅር ወይም አደረጃጀት ሊኖረው ይገባል፡፡

# ንዑስ ክፍል ሁለት

# የውጭ ሃገር የሐይማኖት ተቋም

## 9. ምዝገባ

1. በውጭ ሀገር የተመሰረተና ኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ መክፈት የሚፈልግ የሐይማኖት ተቋም የሚመዘገበው፤

ሀ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ ለመክፈት መፈለጉንና ተወካዩ እንዲሰራ መፍቀዱን የሚገልጽ የሰነድ ማረጋገጫ፤

ለ/ በተመሰረተበት አገር የሚታወቅና ህጋዊ መሆኑን የሚያሳይ ሰነድ (የምስክር ወረቀት)

ሐ/ የሐይማኖት ተቋሙ የመተዳደሪያ ደንብ፤

መ/ ቅርንጫፍ ለመክፈት የሚወከሉት ሰዎች ከሐይማኖታዊ ሥራው ጋር በተያያዘ ከአንድ አመት ያላነሰ ተገቢ የስልጠና ማስረጃ ሲያቀርብ፣

ሠ/ የውጭ ሃገር ዜጋው ፓስፖርትና ቪዛ ሲያቀርብና ሲያሟላ ነው፣

ረ/ በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ የሚከፍተው የሃይማኖት ተቋም አላማ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ውስጥ ያልነበረ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ በሃገር ውስጥ ቢያንስ <u>አንድ መቶ አባላት ያሉት፣</u> አላማውም ከሃገሪቱ ህጎች፣ ከህዝብ ሞራል፣ ባህል እና ስነ ምግባር የማይቃረን መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ለ፣ ሐ እና መ የተመለከቱትና ከውጭ ሃገር የመጡ ሠነዶች በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጡ መሆን አለባቸው፡፡

3. የውጭ ሀገር ዜጎች የሃይማኖትና ዕምነት ተቋም ለመመስረት፡-

ሀ. ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት በተለያየ የስራ ምክንያት ሊሆን ይገባል፤

ለ. የታደሰ ፓስፖርት፣መኖሪያ ፈቃድ እና ስራ ፈቃድ ሲያቀርቡ፣

ሐ.በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኤምባሲ/ቆንሲላ የድጋፍ ደብዳቤ ሲያቀርቡ፣

መ. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 ከተዘረዘሩት ከ "መ" እና "ሰ" በስተቀር ያሉት መስፈርቶች ተሟልተው ሲቀርቡ፣

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 3 የሚመሠረተዉ ተቋም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 24 (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በየዓመቱ የሚታደስ የምዝገባ ሰርትፍኬት ይሰጠዋል፡፡

5. በዚህ መመሪያ መሠረት የሐይማኖት ተቋሙ ከተመዘገበ በኋላ በማናቸውም ምክንያት ሳይሟሉ የቀሩ ጉዳዮች ከተገኙና ከተረጋገጡ ሚኒስቴሩ በሰላሳ የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

6. በንዑስ አንቀፅ 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ከተመዘገበ በኋላ ለምዝገባ ያቀረባቸው ሰነዶች ወይም መረጃዎች ሕገ ወጥ ሆነው ከተገኙና ከተረጋገጡ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ይሰርዛል እንደ የሁኔታው አግባብነት ባለው ህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

## 10. <u>ምዝገባ ስለሚከለከልበት ሁኔታ</u>

1. በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀፅ 5 ተላልፎ ከተገኘ፣
2. ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣6፣7፣8 እና 9 ሥር የተዘረዘሩት አለመሟላታቸውን ካረጋገጠ፣
3. የሐይማኖት ተቋሙ የሚመዘገብበት ስም ወይም ዓርማ/ምልክት ከሌላ ከተመዘገበ የሐይማኖት ተቋም ስያሜ ወይም ዓርማ/ምልክት ጋር የሚመሳሰል ወይም ትርጉሙ ላለመግባባት የተጋለጠ ከሆነ አይመዘገብም፡፡

## 11. <u>ህጋዊ ሰውነት ማግኘት</u>

የሐይማኖት ተቋሙ በሚኒስቴሩ ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት እንደተሰጠው ህጋዊ ሰውነት ያገኛል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## <u>ስያሜ፣ ዓርማ/ምልክት አጠቃቀምና ቅርንጫፍ ስለመክፈት</u>

### 12. <u>ስያሜ፣ ዓርማ/ምልክት አጠቃቀም</u>

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም ስያሜና ዓርማ/ምልክት መጠቀም የሚችለው በሃያ ተከታታይ የስራ ቀናት በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከተደረገና በሚኒስቴሩ ከተመዘገበ በኋላ ነው፡፡

### 13. <u>ስያሜ፣ ዓርማ/ምልክትና መተዳደሪያ ደንብን መለወጥ ወይም ማሻሻል</u>

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. ስያሜ፣ አርማ፤ ማህተም፤ የስራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ መለወጥ ወይም ማሻሻል ይችላል፡፡ ሆኖም በስራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለሚኒስቴሩ ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚደረግ የስም፤ የአርማ፤ የማህተም፣ የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ወይም ማሻሻል የሐይማኖት ተቋሙ የበላይ አካል ውሳኔ እና ለማሻሻል የተፈለገውን ስም፤ አርማ፤ ማህተምና መተዳደሪያ ደንብ ከነመግለጫው በሰነድነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
3. የስያሜና የዓርማ/ምልክት ለውጥ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት የሚኖረው ተደራሽነት ባለው ጋዜጣ ከወጣ በኋላ ነው፡፡
4. የቀረበው የስም፤ የአርማ፤ የማህተም እና የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ ወይም ማሻሻያ በህግ አግባብ ተቀባይነት ሲያገኝ እንዲመዝገብ ይደረጋል፡፡
5. የተመዘገበው የመተዳደሪያ ደንብ የሚኒስቴሩ ማኅተም ተደርጎበት ለተቋሙ ይሰጣል፡፡
6. እንዲመዘገብለት ያቀረበውን የለውጥ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ሚኒስቴሩ የማይቀበል ከሆነ ምክንያቶቹን በመግለጽ በቃል ወይም በጽሁፍ ለአመልካቹ ሊያሳወቅ ይችላል፡፡

### 14. <u>ቅርንጫፍ መክፈት</u>

1. ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም መተዳደሪያ ደንቡን መሰረት በማድረግ ቅርንጫፍ ሊከፍት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ስለሚከፍተው ቅርንጫፍ፤ ቅርንጫፉን ለሚከፍትበት የሚመለከተው የክልል አካል ማሳወቅ፣ ስምምነት ማግኘት፣ የስምምነት

ውጤቱን፣ አድራሻውንና የአመራሮች መረጃ በ30 ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የውጭ ዜጎችን ስለማሰራት

### 15. የውጭ ዜጎችን ማሰራት፣

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. የውጭ ዜጋን ተቀብሎ ማሰራት የሚችለው ግለሰቡ አግባብ ባለው የሀገሪቱ ሕግ መሰረት የስራ ፈቃድ ያገኘ ሲሆን ነው፡፡
2. የሚያሰራው የውጭ ዜጋ ከመጣበት ዓላማ ውጪ እንዳይንቀሳቀስ ተገቢውን ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

### 16. ለስራ ፈቃድ የሚሰጥ የድጋፍ ደብዳቤ ቅድመ ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም ሊያሰራው ለፈለገው የውጭ ዜጋ የስራ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ የድጋፍ ደብዳቤ ሲጠይቅ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡፡

ሀ. የውጭ ዜጋ ለማሰራት እንደሚፈልግ ማመልከቻ ማቅረብ፣

ለ. የውጭ ዜጋው ሊያገለግል የመጣበት ምክንያት ወይም የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት፣

ሐ. ከሐይማኖታዊ ሥራው ጋር በተያያዘ ያለው ከአንድ አመት በላይ የሆነ ተገቢ የስልጠና ማስረጃ ሲያቀርብ፣

መ. ከመጣበት ሀገር አግባብነት ካለው አካል የተጻፈ የድጋፍ ማስረጃ፣

ሠ. የሐይማኖት ተቋሙ የውጭ ዜጋውን የተቀበለው መሆኑን የሚገልጽ የስምምነት ማረጋገጫ

ረ. የውጭ ዜጋው ህጋዊና የታደሰ ፖስፖርት፣

ሰ. ለአገልግሎት የሚቆይበት ጊዜና ቦታ፣

ቀ. ለአገልግሎት በሚቆይበት ጊዜ የሚጠቀምበት ወይም የሚያገኘው የገቢ ምንጭ፣መጠን መገለፅ አለበት፣

በ. የሃይማኖት ተቋሙ ጥያቄውን እስካቀረበበት ጊዜ ድረስ በሐይማኖት ተቋሙ ውስጥ ምን ያህል የውጭ ዜጋ እያገለገለ እንዳለ የሚገልፅ ደብዳቤ፣

ተ. ከላይ በ "ለ" "ሸ" እና "በ" የተዘረዘሩትን በዋናነት ያካተተ ሆኖ ሌሎች አግባብነት ያለቸው ስምምነቶችን የያዘ የስራ ውል፣

2. ጥያቄው ለሥራ ፈቃድ እድሳት ከሆነ፤

ሀ. እንደ ቅደም ተከተላቸው ቀደም ሲል ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ርና ከዜግነትና ኢሚግሬሽን ጉዳዮች መምሪያ የተሠጠ ጊዜው ያላለፈበት የስራ ፈቃድና የመኖሪያ ፈቃድ፣

ለ. ሌሎች በዚህ ንኡስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩት አስፈላጊ መረጃዎች፣

3. የሚቀርቡ ሠነዶች በሙሉ ዋናው ከፎቶ ኮፒ ጋር መቅረብና መገናዘብ አለባቸው፡፡

4. ማናቸውም ከውጭ ሀገር ለማስረጃነት የሚቀርቡ ሠነዶች በሙሉ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተረጋግጠውና በሃገሪቱ የፌዴራል የስራ ቋንቋ ህጋዊ በሆነ አካል ተተርጉሞ መቅረብ አለባቸው፡፡

5. ማንኛውም የውጭ ሃገር ዜጋ ከሃይማኖት ተቋሙ ጋር የነበረውን የቆይታ ጊዜ አጠናቆ ከሃገር ከመውጣቱ ከሃያ ቀን በፊት ተቋሙ ለሚ/ር መስሪያ ቤቱ በፅሁፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡ አለማሳወቅ የህግ ተጠያቂነት ያስከትላል፡፡

## ክፍል አራት

## መብት፣ ግዴታ እና የተከለከሉ ተግባራት

### 17. መብቶች

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. ህገመንግስታዊ የሐይማኖት ነፃነትና መብቱን በአግባቡና በህጋዊ መንገድ የመጠቀም፤
2. አሰራሩን ህጋዊ በሆነ መንገድ የማዘጋጀትና የመምራት፤
3. ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማጽድቅ፤ የማሻሻል፤ የመወሰን፤
4. ቅርንጫፍ የመክፈት፤
5. በግልም ይሁን በሕብረት በተሰጠው የምዝገባ ምስክር ወረቀት መንፈሳዊ የትምህርት ተቋም የመክፈት፤
6. በመረጣቸው አመራሮች የመመራት እንዲሁም የመሻር፤
7. የሃይማኖት ተቋሙ ከፈለገ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ በክፍያ የመውሰድና የመጠቀም፤

8. ከህገ-መንግስቱ፣ ከሌሎች የሃገሪቱ ህጎችና ከመተዳደሪያ ደንቡ የሚመነጩ መብቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## 18. ግዴታዎች

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የመምራት፣የመመራት፤ የማክበርና የማስከበር፤
2. በተከታዮቹ ወይም በአባላቶቹ እና ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን የመስራት፤
3. በሥሩ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ ቅርንጫፎች ህግን ተከትለው እየሰሩ መሆናቸውን የመከታተል፣የመደገፍና ችግሮች ሲያጋጥሙ የማረም፤
4. የገቢ አሰባሰብና የወጪ አስተዳደር በህጋዊ መንገድ መከናወን አለበት፣
5. የሂሳብ አያያዙን በኦዲተር በማስመርመር ለተቋሙ የበላይ አካል አቅርቦ የማጸደቅ፤
6. በሐይማኖት ሽፋን የሚደረጉ ፀረ-ሠላም፤ አክራሪነትና የጽንፈኝነት እንቅስቃሴዎችን የመከላከል፤
7. የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን እንዲሁም የዕድሳት ማስረጃውን በዋናው ጽ/ቤትና በየቅርንጫፎቹ እንዲገኝ የማድረግ፤
8. ህገ-መንግሥቱን፣ ሌሎች የሃገሪቱን ህጎች፣ መተዳደሪያ ደንቡንና ይህን መመሪያ አክብሮ የመንቀሳቀስ ግዴታዎች አሉበት፣
9. የአመራር ውሳኔ ለሚጠይቁ እንደ ባንክ፣ የህትመት ስራዎች፣የስያሜና የአርማ ለውጥ፣ለውልና ሰነዶች፣ለፕሬስና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጠው አካል በተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፣

## 19. የተከለከሉ ተግባራት

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም ከሚከተሉት ተግባራት ራሱንና ተከታዮቹን መከላከል አለበት፡፡

1. ከተቋቋመበትና ከተመዘገበበት ሐይማኖታዊ ዓላማ ውጭ መንቀሳቀስ፣
2. የራሱን ሐይማኖት ሌላ ሰው በግድ እንዲያምን ወይም እንዲከተል ማድረግ ፣
3. ከሐይማኖት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ማስታወቂያዎች፣ ብሮሸሮች፣ መጽሄቶች፣ በራሪ ጽሑፎች በመደበኛ የትምህርት ተቋማት፣ በግልና ህዝባዊ አገልግሎት ለመስጠት ከመንግስት ፈቃድ በተሰጣቸው ተቋማት እንዲሁም በመንግስታዊ ተቋማት ግቢ ውስጥ መለጠፍ፣ በመቀስቀሻነት መጠቀምና ማሰራጨት፣

4. የሌላውን ሐይማኖት ማናናቅ፣ መስደብ፣ ማዋረድ፤ በአማኞች መካከል ግጭትን ሊያስነሱ የሚችሉ መልእክቶችን በሚዲያ ማስተላለፍ፣ፅሁፎችን መፃፍና ማሰራጨት፤
5. በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ አገር ከሚገኙ ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በመቃረን ከሚንቀሳቀሱ አካላት ጋር ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት ማድረግ ወይም በማናቸውም ሁኔታ መርዳት ወይም እርዳታ መቀበል፣
6. ህዝብን ለግጭትና ለህገ-ወጥ ጥያቄ ማነሳሳት፣
7. የውጭ አገር ዜጋን ያለ ሥራ ፈቃድ ተቀብሎ ማሰራት፣
8. የተሰጠውን የምሥክር ወረቀት ለሌሎች አካላት አሳልፎ መስጠት ወይም ህጋዊ ካልሆነ አካል ጋር አብሮ መስራት፤
9. በዚህ መመሪያ መሰረት በተሰጠው የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሐይማኖታዊ ተግባራትን ከበጎ አድራጎት ተግባራት ጋር ቀላቅሎ መሥራት፣
10. ሌሎች በህገ-መንግስቱና በሌሎች የሃገሪቱ ህጎች የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም፣
11. ከቤተ ዕምነትና ሌሎች ከተፈቀዱ ቦታዎች ውጪ ሃይማታዊ ቅስቀሳዎችን ማካሄድ
12. የሃይማኖት ተቋሙን ህጋዊ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ አስይዞ ከማንኛውም የፋይናንስ ተቋም ብድር መበደር ናቸው፡፡
13. ከላይ የተዘረዘሩትን ክልከላዎች ተላልፎ የተገኘ ተቋም ወይም ግለሰብ አግባብ ባላቸው የሃገሪቱ ህጎች ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አምስት

## ሪፖርት ፣ ዕድሳት፣ ክትትልና ድጋፍ እና ህጋዊ ሰውነትን ማጣት

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ሪፖርት ማድረግ

### 20. ዓመታዊ የሒሳብ ምርመራ ስለማድረግ

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. ሒሳቡን በየዓመቱ በተፈቀደለት ህጋዊ የውጭ ኦዲተር ወይም በተቋሙ የበላይ አካል በተመረጠ የውስጥ ኦዲተር ማስመርመር አለበት፡፡
2. በውጭ ኦዲተር የማስመርመር ግዴታ የሚኖርበት በበጀት ዓመቱ ያንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠን ከብር 500, 000.00 (አምስት መቶ ሺ) እና በላይ ሲሆን ነው፡፡

3. ገንዘቡ ከብር 500, 000.00 (አምስት መቶ ሺህ) በታች ከሆነ የሚመረመረው በተቋሙ የበላይ አካል  በተመረጠ የውስጥ ኦዲተር ይሆናል፡፡
4. በውጭ ኦዲተር የሚመረመር የኦዲተር ሪፖርት በሕጋዊ መንገድ ተወዳድሮ ባሸነፈ ገለልተኛ ኦዲተር መሆን አለበት፡፡
5. የኦዲት ሪፖርቱ ፡-

ሀ. የሂሳብ መዛግብቱና መግለጫው፣ የተቋሙን ገቢና ወጪ፣  ሃብትና የዕዳ ሁኔታ የሚያሣይ፣

ለ. የሚያስተዳድራቸው ተቋማትን በማከራየት እና በቅጥር የሚያሰራቸውን ሠራተኞች የገቢና የሥራ ግብር ገቢ  መደረጉን/ መከፈሉን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

6. የሒሳብ መግለጫና ተያያዥ ሰነዶች የበጀት ዓመቱ ካበቃበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአስር ዓመታት ተጠብቀው ሊቆዩ ይገባል፡፡

## 21. ዓመታዊ የስራ ክንውን፣ የኦዲት ሪፖርትና ዕቅድ ማቅረብ

1. ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም እንደ የበጀት ዓመቱ አቆጣጠር በየዓመቱ ለሚኒስቴሩ ፡-

ሀ. በአንቀጽ 20 መሰረት የተመረመረ ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት፣

ለ. የቀጣይ ዓመት ዕቅድ ከነበጀት ክፍፍሉ እና የበጀት ምንጩን ፣

ሐ.በስራ ላይ የሚገኙ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ዝርዝር፣ የሃይማኖት ተቋሙ የአጥቢያ፣ ቅርንጫፍና የተከታዮች ብዛት የሚገልፅ፣

መ. የስራ ክንውን ሪፖርት  እና የተቋሙ የበላይ አካል ያፀደቀበት ቃለ ጉባኤ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

2.ሪፖርቶች መቅረብ ያለባቸው፤

ሀ. በውጭ ኦዲተር ለሚያስመረምሩ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ፣

ለ. በውስጥ ኦዲተር ለሚያስመረምሩ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

## 22. የባንክ ሂሳብን መክፈትና ማሳወቅ

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. ህጋዊ ሠውነት ባገኘ በሶስት ወራት ውስጥ  በስሙ የባንክ ሂሳብ መክፈት ይኖርበታል፡፡

2. ለባንክ የድጋፍ ደብዳቤ እንዲፃፍለት ሲጠይቅ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ሂሳቡን የሚያንቀሳቀሱ አመራሮች መመረጣቸውን የሚያረጋግጥ ቃለ ጉባኤ ሲያቀርብ ይፃፍለታል፡፡

## 23. <u>የስራ መሪዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

1. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የተመረጡ የመሪዎችና የሥራ ኃላፊዎችን ዝርዝር መረጃ መዝግቦ መያዝና ከዓመታዊ የስራ ሪፖርት ጋር ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚያዘው መረጃ የተቋሙ የበላይ አካል እና በዋና ፅሕፈት ቤት በየደረጃው ያሉ የአመራሮች ስም፣ዕድሜ፣ዜግነት፣የመኖሪያ አድራሻ፣ ስልክ ቁጥርና የኃላፊነት ድርሻ ይሆናል፡፡

## <u>ንዑስ ክፍል ሁለት</u>

## <u>ዕድሳት ማድረግ</u>

## 24. <u>ዕድሳት</u>

1. የሀገር ውስጥ የሐይማኖት ተቋም የምዝገባ ፈቃዱን <u>በየአምስት</u> ዓመቱ ማሳደስ አለበት፡፡
2. የውጭ ሀገር የሐይማኖት ተቋም <u>በየዓመቱ</u> የምዝገባ ፈቃዱን ማሳደስ አለበት፡፡

## 25. <u>ለዕድሳት መሟላት የሚገባቸው ሰነዶች</u>

1. የምዝገባ እድሳት እንዲደረግለት የሚጠይቅ ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፡-

   ሀ/ የእድሳት መጠየቂያ ማመልከቻ፤

   ለ/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 21 መሰረት የበጀት ዓመቱን ዓመታዊ የስራ ክንውንና የኦዲት ሪፖርት ፤

   ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት አግባብነት ባለው አካል የተሾሙ ወይም የተመረጡ እንዲሁም የተመደቡ አመራሮችና የሥራ ኃላፊዎች የሹመት ወይም የምርጫ ቃለ-ጉባኤ፤

   መ/ ጉዳዩን እንዲያስፈጽም የተወከለው ግለሰብ ከሐይማኖት ተቋሙ አግባብነት ባለው አካል መወከሉን የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

2. እድሳት የሚደረገው የሐይማኖት ተቋሙ የተፈቀደለትን ዓላማ ለማሳካት ህግን ተከትሎ የሰራና የቀረቡት ሰነዶች በትክክል የተዘጋጁ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

3. የምዝገባ እድሳት ጥያቄ መቅረብ ያለበት ቀደም ሲል የተሰጠው የዕድሳት ጊዜ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት መሆን አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ክትትልና ድጋፍ

### 26. ክትትልና ድጋፍ

1. ሚኒስቴሩ ከልዩ ልዩ አካላት የሚቀርቡለትን ሪፖርቶች፣ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች መነሻ በማድረግ በምስረታ ላይ ባለ ወይም በተመዘገበ የሐይማኖት ተቋም ላይ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ድጋፍና ክትትል የሚሹ የትኩረት ጉዳዮች፡-

ሀ. በሃይማኖት ተቋማት ውስጥና መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን፣ ሃይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የአክራሪነት/ፅንፈኝነት ሁኔታዎች፣ አለመግባባቶችንና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለማረምና ለማስተካከል፣ ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥ፣

ለ. የገቢ ምንጭ መሠረቱንና ገቢውን ለታለመለት አላማ ስለመዋሉ፣

ሐ. በተቋቋመለት አላማ ስለመንቀሳቀሱ፣

መ. አስፈላጊ ሪፖርቶችና መረጃዎች በወቅቱ ስለማቅረቡ እና ሲጠየቅም ምላሽ ስለመስጠቱ፣

ሠ. ወቅቱን የጠበቀ ዕድሳት ስለማድረጉ፣

ረ. ህግን አክብሮ ስለመንቀሳቀሱ፣

ሰ. በዚህ መመሪያ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ስለማሟላታቸው ይሆናል፡፡

### 27. የማስተካከያ እርምጃ

ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 26 መሠረት የሚያደርገውን ክትትል መነሻ በማድረግ፤

ሀ. በህግና በልዩ ልዩ አሰራሮች ላይ ግንዛቤ በመስጠት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ለ. እንደአስፈላጊነቱ የተደረገውን ምዝገባና የተሰጠውን ህጋዊ ሠውነት ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል፡፡

ሐ. የህግ ጥሰት ተፈጽሞ ከተገኘ አግባብነት ባለው ህግ እንዲጠየቅ ይደረጋል፡፡

መ. አጠቃላይ የስራ ክንውን ሪፖርት ለአንድ አመት ያላቀረበ የፅሁፍ ማስጠንቂያ በመስጠት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲያሟላ ይደረጋል፣ በዚህ ጊዜ ገደብ ካላሟላ

ይታገዳል ከታገደበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተቋሙ ዋና መስሪያ ቤት ከሚገኝበት ወረዳ ወይም ዞን ወይም ክልል የድጋፍ ደብዳቤና ያላሟላውን ሪፖርት ካልቀረበ የህጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

ሠ. የዕድሳት ዘመኑ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ሪፖርት ያደርጋል፣ በዚህ ጊዜ ገደብ ካልቀረበ ይታገዳል፣ ከታገደበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የተቋሙ ዋና መስሪያ ቤት ከሚገኝበት ወረዳ ወይም ዞን ወይም ክልል የድጋፍ ደብዳቤና ለዕድሳት አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን አቅርቦ ካላሳደሰ የህጋዊ ሰውነት የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## ህጋዊ ሰውነትን ማጣት

### 28. ህጋዊ ሰውነትን ማጣት

የሐይማኖት ተቋም ህጋዊ ሰውነት ከሚከተሉት በአንዱ አካል ሊያጣ ይችላል፡-

ሀ. በሐይማኖት ተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የበላይ አካል ሲወሰን፣

ለ. በፍርድ ቤት ሲወሰን፣

ሐ. በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 19 የተዘረዘሩትን ተግባራት ፈፅሞ ሲገኝና በሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ሲወሰን፡

## ክፍል ስድስት

## የአገልግሎት ክፍያ፣ ያለመግባባቶች አፈታትና ቅሬታ አቀራረብ

### 29. የአገልግሎት ክፍያዎች

1.ሚኒስቴሩ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች በሚኒስትሮች ም/ቤት በፀደቀው የክፍያ ተመን ሰንጠረዥ መሠረት ያስከፍላል፡፡

2. በዚህ መመሪያ መሠረት ሚኒስቴሩ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

ሀ/ አዲስ ምዝገባ

ለ/ ዕድሳት እና

ሐ/ ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች ናቸው፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) መሠረት የሚሰጡት አገልግሎቶች

ሀ/ ለአርማና የስም ለውጥ የድጋፍ ደብዳቤ፣

ለ/ መተዳደሪያ ደንብና የምስክር ወረቀትን ጨምሮ አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች ፎቶ ኮፒ፣

ሐ/ የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ መመዝገብ፣

መ/ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ለሚፈልጉ አካላት አገልግሎት መስጠት ናቸው፡፡

## 30. ምትክ ማስረጃ ስለመስጠት

1. ቀደም ሲል በህጋዊ መንገድ ተሰጥቶት የነበረው ማስረጃ በተለያዩ ምክንያቶች የጠፋበት ወይም ተገቢውን የአስረጂነት አገልግሎት በማይሰጥ ሁኔታ የተበላሸበት የሐይማኖት ተቋም በድጋሚ እንዲሰጠው ማመልከት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ መሠረት ማስረጃ ማለት የምዝገባ፣ የዕድሳት፣ የድጋፍ ደብዳቤዎች ወይም የመተዳደሪያ ደንብን የሚመለከት ሠነድ ነው፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በጠፋው ማስረጃ ምትክ ሊሰጠው የሚችለው፡-
   ሀ. ማስረጃው ስለመጥፋቱ ወይም ስለመበላሸቱ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት በሚመለከተው አካል ከነምክንያቱ ካረጋገጠ እና ምትክ ማስረጃ እንዲጠየቅ መስማማቱን የሚገልፅ የፀደቀ ቃለ-ጉባኤ፣
   ለ. ምትክ ማስረጃ የተጠየቀው ለተበላሸና የማያገለግል ከሆነ የተበላሸውን ማስረጃ ማቅረብ፣
   ሐ. የሐይማኖት ተቋሙ ከሚገኝበት አካባቢ ካለው የፖሊስ አካል ማስረጃው የጠፋበት ስለመሆኑ የተሰጠ የፅሁፍ ማስረጃ፤
   መ. ጉዳዩን እንዲያስፈጽምና የተጠየቀውን ሠነድ እንዲረከብ አግባብነት ባለው አካል የተሰጠ ውክልና ማስረጃ ሲቀርብ ነው፡፡

## 31. የአለመግባባቶች አያያዝና አፈታት

1. ማንኛውም የሐይማኖት ተቋም ከሌላ የሐይማኖት ተቋም፣ በአመራሩና በአባላቱ ወይም በአባላቱ መካከል አስተዳደራዊ አለመግባባቶችና ቅሬታዎች ሲከሰቱ፤
   ሀ/ በሐይማኖታዊና በሰላማዊ ውይይት አለመግባባቶችን በመፍታት ለችግሩ መፍትሔ መስጠት፣
   ለ/ ጉዳዩን በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለበላይ አካሉ በማቅረብና በመወያየት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፡፡

2 የአለመግባባቱ ወይም የቅሬታው ጉዳይ መፍትሔ እንዲያገኝ ለሚኒስቴሩ ከቀረበ የችግሩ ምክንያትና መነሻ ምን እንደሆነ በተለያዩ መንገዶች በማስረጃ በማጣራት፣

ሀ/ ያልተግባቡትን ወገኖች በአካል በመጥራት፣ በማወያየትና የመፍትሔው አካል በማድረግ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታትና ለማስማማት ይጥራል፣

ለ/ ጉዳዩ ለሐይማኖት ተቋሙ የበላይ አካል ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ውሳኔ እንዲያገኝ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱም ሂደቱን በታዛቢነት ሊከታተል ይችላል ወይም

ሐ/ ጉዳዩ በሁለቱም ወገኖች ስምምነት በእርቅ እንዲያልቅ በሚመርጡት ገለልተኛ አካል መፍትሔ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

3. ከላይ በተቀመጡት አማራጮች መሠረት ችግሩ መፍትሔ ካላገኝ ፍላጎት ያለው ወገን ጉዳዩን ለሚመለከተው የፍትህ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

## 32. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

1. ሚኒስቴሩ ከምዝገባ፣ከዕድሳትና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዲሁም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ጋር በተገናኘ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም አካል ቅሬታውን ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት ማቅረብ ይችላል፡፡ በመሆኑም ቅሬታው የተፈጠረው፡-

   ሀ. ባለሙያ በሰጠው አገልግሎት ላይ ከሆነ ለቅርብ ኃላፊው፣

   ለ. የቅርብ ኃላፊው በሰጠው አገልግሎት/ ውሳኔ ላይ ከሆነ ቀጥሎ ላለው የቅርብ ኃላፊ፣

   ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) መሠረት በተሰጠ ውሳኔ ላይ ከሆነ ለሰብዙሃንና ሙያ ማህበራትና የሃይማኖትና ዕምነት ጉዳዮች ሚኒስትር ዲኤታ፣

   መ. ለዚህ መመሪያ አፈፃጸም ሚኒስትሩ የሚሰጡት ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 /ሀ - ሐ/ በተመለከተው መሠረት የሚቀርበው ቅሬታ በፅሁፍ ሆኖ የቅሬታውን ዝርዝር ምክንያት፣ ቀን፣ ስምና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡

3. ከላይ ከሀ - ሐ በተመለከተው መሠረት ቅሬታዎቹ ለሚመለከተው አካል መቅረብ ያለባቸው የቅሬታው ምክንያት በተፈጠረ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ መሆን አለበት፡፡

4. ቅሬታው የቀረበለት በተዋረድ ያለ ውሳኔ ሰጪ አካል ለቀረበለት ቅሬታ እንደ ጉዳዩ ይዘትና ሁኔታ ውሳኔውን ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 33. የልዩ ልዩ አካላት ግንኙነቶች

1. ሚኒስቴሩ ሀይማኖትን ሽፋን ያደረጉ የአክራሪነት/የጽንፈኝነት አመለካከትና ተግባራትን በመከላከልና በመታገል ከማንኛውም አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡
2. በህገ-መንግስቱ የተቀመጠው የሃይማትና የመንግስት መለያየት እንደተጠበቀ ሆኖ በሀገር ሰላም፣ በህዝብ ደህንነት፣ በልማት እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ጉዳዮች ላይ በጋራና በትብብር ይሰራል፡፡

### 34. ውክልና ስለመስጠት

ሚኒስቴሩ በአዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለማስፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት አግባብነት ላለው የፌደራል ወይም የክልል አካል ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

### 35. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጐች

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 36. መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

### 37. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 01 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**

**ጥር 2010 ዓ.ም**

**ከበደ ጫኔ**

**የፌደራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች**

**ሚኒስቴር ሚኒስትር**